# Legacy International Spiritual Ministry

# 2018 GC Annual Summary Report



**Legacy International Spiritual Ministry**
**P.O.Box 192/1070**
**Cell # 251 930 651943**
**Act: #; Berhan Bank 2600010008458**
**Addis Ababa, Ethiopia**

***ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!***

***ጉዳዩ፡ የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2018 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ***

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት የሁለተኛ ዓመቱን ጠቅላላ ጉባዔ ጥር 18፣ 2011 ዓም (January 26፣ 2019) ባደረገበት ወቅት ሪፖርት እንደተደረገው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ዘንድ ብዙም ትኩረት ያልተሰጠውን ትዉልድ ክፍተት በማየት አገልግሎቱ ፋና ወጊ ተግባራትን በእግዚአብሔር እርዳታ ማከናወን እንደቻለ የተገለጸ ነዉ። አገልግሎቱ ራዕዩን እውን ለማድረግ በቅድሚያ ‹‹**በትንሹ መጀመር**›› በሚል የአደረጃጀት መርሆና ‹‹**እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ እንዳይነሳ**›› በሚል አንኳር መልእክት በማንገብ ሥራውን መጀመሩ ይታወሳል ።

የአገልግሎቱ ቦርድ መልካም አመራር የሰጠ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ዉስጥ ለጠቅላላ ጉባዔ የነበረዉን ዝግጅት ጨምሮ ሶስት መደበኛ ስብሰባዎች አድርጓል። በእነዚህ ስብሰባዎቹ ቦርዱ በልዩ ልዩ አጀንዳዎች ላይ አመርቂ ውይይት በማድረግ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ አቅጣጫ ሰጥቷል። በዓመቱ ውስጥ አገልግሎቱን የማስተዋወቅ፣ ድጋፍ የማሰባሰብ፣ የግንኙነት መረብ የማጠናከር ሥራዎች የቀጠሉ ሲሆን በጎ ፈቃደኞች በገንዘባቸው፣ በጊዜያቸው፣ በእውቀታቸውና በሀብታቸው ከዚህ አገልግሎት ጎን ለመቆምና አብሮ ለማገልገል በገቡት ቃል መሠረት አገልግሎቱን የመደገፍ ሥራዎች ተሠርተዋል። ከዚህም የተነሳ በእግዚአብሔር ጸጋ ሌጋሲ የበጎ አገልጋዮች ዉጤት ነዉ ማለት ይቻላል። የአገልግሎቱ አንኳር ተግባር የሆነዉን ሥልጠና የመስጠት ሥራ ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በእቅዱ መሠረት ማከናወኑ አርአያነቱ እንዲቀጥል አድርጓል። በመሆኑም **1ኛወጣቶች በተመለከተ፡ ከቃለ እግዚአብሔር አንባቢያን ማኅበር** ጋር በመተባበር January 31, 2018 ‹‹የጥሞና ጊዜ›› ላይ ሥልጠና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ክርስቲያን ተማሪዎች መሪዎች ሰጥቷል። በሥልጠናው **ወደ 150 ተማሪዎች** ተካፍለዋል። ስለወጣቶች **ተግዳሮቶች** እና መፍትሔዎቻቸው እንዲሁም **በአምስት የወጣት ሕይወት መንፈሳዊ ምሰሶዎች** ላይ **(መዳን፣ መመሥረት፣ መግባባት፣ መታደስ፣ መሸከም)** ‹‹በልዩነት የተገለጠ ክርስቲያናዊ ወጣት›› በሚል መሪ ሃሳብ ሥር የወጣትነት ማንነት፣ ግኑኝነት፣ መንፈሳዊ አቋምና ዓላማ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ከመሪ መካነ የሱስ ማህበረ ምዕመናን እንዲሁም ከደሴ፣ ከደብረማርቆስ፤ ከሀረር፣ ከእንጂባራ እና ከሃዋሳ ሙሉ ወንጌል ቤ/ክ ጋር በመተባበር **ለ389** ወጣቶች በግንባር ተሰጥቷል። በተጨማሪ በሀረርና በሃዋሳ የግል ጊዜ ከጌታ ጋር በሚሉ ርዕሶች ላይ ለወጣቶቹ ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን በሀረርም **ትዳርን በመልካም ስለመጀመር** ሥልጠና ተስጥቷል።





**የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2018 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ**

2ኛ ‹‹እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ እንዳይነሳ›› በሚል መሪ ሃሳብ ሥር **ለ341** ወላጆች **በሰባት መንፈሳዊ ምሰሶዎች (ማስተዋል፣ ማዳን፣ ማስመለጥ፣ ማሳየት፣ ማስጠንቀቅ፣ ማስረከብ፣ ማስተላለፍ)** እንዲሁም **መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ** በሚል ርዕስ ዙሪያ ከላይ በተጠቀሱ በታዎች ናዝሬት ገንደ ጋራ ወንጌል ጋራ ወንጌል ጨምሮ ሥልጠና ተሰጥቷል።




**ኢየሱስ ጌታ ነዉ**

**ክብር ለርሱ ነዉ ይገባል!!!**







**3ኛ፣** እግዚአብሔርን የማያውቅ ትውልድ እንዳይነሳ›› በሚል መሪ ሃሳብ ሥር ከአዲስ አበባ ዉጭ ለሚገኙ አራት አጥቢያዎች እና አዲስ አበባ መሪ መካነ የሱስ ለሚገኙ **176 የ**ቤ/ክ መሪዎች ትዉልዱን ማስመለጥ በተመለከተ **ደወል** የማሰማት ሥራ ተሠርቷል።

**4ኛ የወጣቶች አሠልጣኞች ሥልጠና**

ከሳሪስ ወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር ለ**14** አሠልጣኞች፣ ከኢቫሱ ጋር በመተባበር **ለ190** ዩኒቬርስቲ ተማሪዎች በግል ጥሞና ጊዜ ላይ (በደብረ ዘይት) በድምሩ **ለ204** የወጣቶች አሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል። ለክትትል እንዲረዳም ተግባራዊ ዕቅድ አዘጋጅተዉ ሄደዋል። በተለይ የጥሞና ጊዜ በተመለከተ በቅድም እና ድህረ ሥልጠና በተደረገ አሰሳ ሠልጣኞች ለዉጥ ማሳየታቸዉ፣ ብዙዎች የጥሞና ጊዜ ለመዉሰድ መወሰናቸዉ ለማወቅ ትችሏል። በጠቅላላዉ በግንባር የተከናወነዉ **ለ1056 ሰዎች** ሲሆን የአሠልጣኞች ሥልጠና(204) ሲጨምር ለ**1260** ነዉ። በሳሪስ የተደረገዉን የወጣቶች አሠልጣኞች የማዉረድ ሥራ (**ለ60**) ሲጨምር ደግሞ አጠቃላይ የተከናወነዉ ለ**1320** ተሳታፊዎች ነበር።









እአአ 2018 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይዞ የነበረው በጀት ብር **840280.00** ሲሆን የተሰበሰበዉ ገቢ ብር **179,746.62**፣ አጠቃላይ ወጪ ብር **188486.15** ነበር፤ ካለፈዉ ዓመት የዞረዉ ከወጪ ቀሪ ብር **52962.16** ታስበና ወጪዉ ተሰልቶ፣ በ2018 መጨረሻ ላይ ወደሚቀጥለዉ ዓመት የዞረ ብር **44222.63** መሆኑ በኦዲተር ተረጋግጦ ለጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቷል። በቀጣይነትም የጥሪት ማሰባሰብ ሥራዉ ተጠናክሮ በትኩረት እንዲከናወን ማሳሰቢያ ተሰጥቶበታል። እአአ ለ2019 ዓም ለአገልግሎቱ ብር **1049220.00** በጀት ጸድቋል። **በማጠቃለያም** አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆም በትጋት ለተንቀሳቀሱ በተለይ ቢሮ ስለሰጡ ቤተሰብ፣ በራቸዉን በመክፈት በትብብር እየሠሩ ላሉ (አአ ዉስጥ፣ ከአአ ዉጭ) አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ ኤስ አይ ኤም ስብሰባ በሚኖረን ጊዜ ሁሉ ቦታ ስለፈቀደልን፣ የፌዴራል መንግሥት ፈቃድ ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንዲቻል ስላደረገ፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በዚህም ሪፖርት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም የ2018 አገልግሎት ሂደት እንቅስቃሴ የሚያሳዩ ልዩ ልዩ ፎቶግራፎች በመጎብኘት ጉባዔው ተጠናቋል፣ ዜናዉም በኤልሻዳይ ቴሌ ቪዥን ተላልፏል። ***ለዚህ አገልግሎት መሳካት የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ።***